ለደቡብ ኢትዮጵያ ፀረ ሙሰና
አርባምንጭ

ጉዳዩ፦ በመንግስት ተቋም ውስጥ እየተካሄደ ሰላለው ከፍተኛ የሙሰና ወንጀል ጥርጣሬ ላይ ጥቆማ መስጠትና ተጠያቂው አካል በህግ የሚጠየቅበት አሰቸኳይ ምርመራ እንድደረግ ሰለማሳወቅ ይሆናል።

በዋንጫ ሽልማት ጭምብል ውስጥ የተደበቀውና በጋሞ ዞን ጨንቻ አጠቃላይ ሆስፕታል ከፍተኛ የሥራ ሀላፊዎችየተቋሙ ሥራ አስኪያጅና ሜድካል ዳይረክተሩ እና በተባባሪዎቻቸው አማካይነት የተቋሙን ህልውና ከመፈታተንም አልፎ የአገልግሎት አሰጣጡን ከቀን ወደ ቀን እያመሰቃቀለ ያለ፤ በህዝብና መንግስት ሀብት ላይ እየተደረገ ያለ ህገወጥ የፋይናንስ አሰራር ጥሰት ላይ የተመረኮዘ እንድሁም የትርፍ ሰዓት አከፋፈል ላይ የተደረገ ማጭበርበርን የሚያጋልጥ መረጃ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይቀርባል፦

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር መሠረት ከባድ የሙስና ወንጀል ተጠያቂነትንና ቅጣትን ከሚያስከትሉ ጉዳዮች አንፃር፣ በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ ከተፈቀደው መመሪያ ውጪ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አድልዎ በማድረግ ክፍያ መፈፀም እንዲሁም በወሊድ ወይም የዕረፍት ፈቃድ ላይ በመሆን ምክንያት በሥራ ገበታ ላይ በሌሉ ባለሙያዎች ስም የሐሰት ሰነድ አዘጋጅቶ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈፀም አንዱ ነው።

የተጠያቂነቱ ህጋዊ አካሄድ ከ ዋና ዋና አቅጣጫ ይዳሰሳል፦

ኛ፣ ከላይ በተጠቀሰው የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር ሥር አንቀጽ ላይ ሥልጣንን አላግባብ መገልገል በሚለው መሠረት የሆስፒታሉ ኃላፊዎች የተሰጣቸውን የመንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነት በመጠቀም፣ ሕጋዊ አሠራርን በመጣስ ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማስገኘት ድርጊቱን በመፈጸማቸው በዚህ አንቀጽ ያስጠይቃል።

ኛ፣ በአንቀጽ ላይ በመንግሥት ሥራ ላይ እምነት ማጉደል ከሚል አኳያ የመንግሥት የሕዝብ ሀብትና ገንዘብ የሆነውን የሆስፒታሉን በጀት ላላገለገሉበትና ላልተሠራ ሥራ ማዋል በቀጥታ በከባድ እምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን ያስጠይቃል።

ኛ፣ በዚያው አዋጅ አንቀጽ ላይ የሕዝብ ወይም የመንግሥት ሰነዶችን ማጭበርበርበርሐሰት ማዘጋጀት መሠረት በሥራ ላይ የሌሉ ሰራተኞችን ሰርተዋል በማለት የትርፍ ሰዓት መገኘት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ወይም የክፍያ ሰነድ ላይ የሐሰት መረጃ መሙላት ወይም ማጽደቅ ከባድ የሰነድ ማጭበርበር ወንጀል ነው።

ሌላው ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በዚህ የወንጀል ሰንሰለት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፉ ሁሉም አካላት እንደየድርጊታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በሀሳብ በማበር ወይም በጥቅም ተካፋይነት ይጠየቃሉ። ለምሳሌ፦

ሀ፣ ክፍያውን የፈቀዱ፣ ሪፖርቱን እያወቁ ያጸደቁ ወይም የቁጥጥር ግዴታቸውን ሆን ብለው ችላ ያሉ ኃላፊዎች።

ለ፣ ባለሙያዎቹ በወሊድ ወይም በፈቃድ ላይ መሆናቸውን እያወቁ የትርፍ ሰዓት መርሃ-ግብር ያወጡና ድርጊቱ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ የሐሰት መገኘት ፎርም የፈረሙ ግለሰቦች።

ሐ፣ ሰነዶቹ የሐሰት መሆናቸውን እያወቁ ወይም ከተፈቀደው መመሪያ ውጭ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አድልዎ ተደርጎ ክፍያውን ያዘጋጁና ገንዘቡን ፈሰስ በማድረግ የከፈሉ የፋይናንስና ሂሳብ ክፍል ባለሙያዎች።

መ፣ አልሠራንበትም ወይም ፈቃድ ላይ ነበርን ማለት ሲችሉ ነገር ግን እያወቁ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥቅም የተቀበሉ ወይም ስማቸው ተለይቶ ያለአግባብ የተከፈላቸው የጤና ባለሙያዎችም በሙስና ወንጀል ተባባሪነት ወይም የማይገባ ጥቅም በማግኘት ይጠየቃሉ።

ከፍ ሲል በተመለከተው የህግ ድንጋጌ ስር የሥራ ኀላፊዎችንና ባለሙያዎችን ለማስጠየቅ የሚያስፈልጉ ወሳኝ ማስረጃዎችም፦

ኛ የፈቃድና የስምሪት ሰነዶች፦ ባለሙያዎቹ በወሊድ ወይም በተለያየ ፈቃድ ላይ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ የፈቃድ መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጾች፣ የሕክምና ማረጋገጫዎች ወይም የሆስፒታሉ የሠራተኛ አስተዳደር ወይም የሰው ሀብት መዝገቦች።

ኛ የተረኝነትና የ ቅጾች፦ ክፍያ የተፈጸመባቸው የሐሰት የትርፍ ሰዓት መፈረሚያ ወረቀቶች፣ የዕለቱ የክትትል መዝገብ እና የፈረቃ መርሃ-ግብሮች።

ኛ የፋይናንስና ክፍያ ሰነዶች፦ በየወሩ የተዘጋጁ የክፍያ ሰነዶች ፣ የባንክ ሒሳብ ማዘዣዎች
እና ገንዘቡ ወደ ግለሰቦቹ ሒሳብ የገባበት የባንክ መግለጫ ።

ኛ መመሪያዎችና ማኑዋሎች፦ በሥራ ላይ ያለ የመንግሥት ጤና ተቋማት ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት መመሪያ። ይህ ሰነድ
የተፈቀደውን የሰዓት ገደብና አሠራር ለማሳየት ያገለግላል።

ኛ የኦዲት ግኝት።

ኛ የሰው ምስክርነት፦ አብረው የሚሰሩና በዕለቱ ተረኛ የነበሩ ሌሎች የጤና ባለሙያዎች፣ የሆስፒታሉ ታካሚዎች መዝገብ
የሕክምና ካርድ ላይ የፈረመው ትክክለኛ ባለሙያ ማን እንደሆነ ለማረጋገጥ እና የኦዲት ባለሙያዎች ምስክርነት።

በተለይም በዓመት እረፍት እና በወሊድ ፈቃድ ላይ የሚገኙ የሆስፒታሉ
ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓት ሥራ ላይ ሳይገኙ ዲዩቲ ክፍያ ገንዘብ ተሰብስቦ ለዓመታት በድምር ብር፣ በየወሩ
ብር፣ በዓመት ሚሊዮን ብር ወደ ግለሰብ አካውንት እንደተላለፈ የሚያመለክት መረጃ ከሆስፒታሉ እየወጣ ስለሆነ
የሚመለከተው አካል ጉዳዩን እንድያጣራ ያስፈልጋል።

ይህ አሰራር ከሆስፒታሉ የዲዩቲ ክፍያ አከፋፈሉና ገንዘቡ ወደ ግል አካውንት ከተለያዩ ባለሙያዎች ገቢ መሆኑና አለመሆኑ ማረጋገጥ
ይፈልጋል። ስለሆነም የሚመለከተው አካል ቀጥሎ ባለው ዝርዝር መሠረት ምርመራ እንድያደርግ፦

የዲዩቲ ክፍያ የተፈጸመበትን ጊዜና የቦርድ ውሳኔ መዝገብ እንዲመረመር፤

በዓመት እረፍትና በወሊድ ፈቃድ ላይ ከነበሩ ሠራተኞች ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ክፍያዎች እንዲረጋገጡና፣ ገንዘቡ በማን በኩል፣
ለምን ዓላማ እና ወደ የትኛው አካውንት እንደተላለፈ እንዲጣራ፤ የግል አካውንት ጥቅም ላይ ውሎ ከሆነ ይህ ከሥራ እና ከፋይናንስ
ሕግና ሥርዓት ጋር ስለማይጣጠም እንዲጣራ፤

ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ ያላቸው ሰራተኞች በተመሳሳይ ወይም በተለያዩ ስራ ሂደት ውስጥ እየሰሩ
የተጋነነ ልዩነት ያለው ክፍያ ተፈፅሞ ወደ ግለሰብ አካውንት ገንዘብ ገቢ መሆኑንና አለመሆኑ እንድጣራ።

አንዳንድ የስራ ሂደት አስተባባሪዎች ወሩን ሙሉ የትርፍ ሰዓት ስራ ሳይሰሩ እና መደበኛ የስራ ሂደታቸው ላይ ሳይገኙ የወሩን ሙሉ
የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈፀም ወይም ከሰሩት በላይ የተጋነነ ልዪነት ያለው ክፍያ መፈፀም።

የማኔጅመንት አባላት ከሚያውቃቸው ውሳኔዎች ውጪ ለአንዳንድ ልዩ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ ቢሰሩም ባይሰሩም
የወሩን ሙሉ ትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈፀም።

በተቋሙ ሳይገኝ እንዲሁም መደበኛ ስራ ላልሰራ ሰራተኛ በዝምድና የወር ሙሉ ወይም ከፍተኛ የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ ተፈፅሞ
ገንዘቡ ወደ ግለሰብ አካውንት ገቢ መሆኑና አለመሆኑ እንድጣራ።

የስራ ሂደት ኃላፊዎች በእያንዳንዱ ስራ ሂደት በወጣው የትርፍ ሰዓት ስራ ፕሮግራም መሰረት ትክክል መሆኑን አምነው ፈርመው
ያስገቡትን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወደ ግን በመተው ለአንዳንድ ሰራተኛ በዘፈቀደ ከፍ ያለ የተጋነነ ክፍያ ተፈፅሞ ወደ ግለሰብ አካውንት
ገንዘብ ማስተላለፍ።

እናም ከላይ የተገለፁ ዐይነት አስቀድሞ በተዘጋጀውና በተጠና መንገድ በጥቅም ትስስር በተሳሰሩ አካለት ትብብር የተሰራውን
የተበለሻሸ ዝርክርክ ህገወጥ አሰራርን በተመለከተ ዕርምት እንድያደርጉ ከሆስፕታሉ ማህበረሰብ የተለያየ መልዕክት በተደጋጋሚ
ቢደርሳቸውም ከመታረም ይልቅ የፊትህ ጠያቂ የሆስፕታሉ ሠራተኞችን በማሸማቀቅ፣ በማመናጨቅ፣ በመሳደብ፣ የተለያየ ዛቻና
ማስፈራሪያ በማከታተል ለማስቆም ስባል ረጅም መንገድ ከመጓዛቸውም አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ ኢመደበኛ አስቸኳይ የሠራተኞች
ስብሰባ በመጥራት እና ለስብሰባው ንግግር አስቀድመው የመለመሏቸውን ወይም ያደራጇዋቸውን የጥቅም ተጋሪ የሆኑ ተባባሪ
የወንጀሉ ተጠሪጣሪ ግለሰቦችን ብቻ በየስብሰባው በማስጮህ የጨቀዬ አሰራራቸውን ለማዳፈንና ጉዳዩ ወደ ሚመለከተው አካል
ይደርስ ይሆናል በሚል ፍራቻ ስህተትን በስህተት ለማጣፋት ስባል የተሰብሳቢውን የእጅ ስልክ በመቀማት ዝግ ስብሰባ እስከማድረግ
ተደርሷል።

ከጆሮዬም በላይ ዐይኔን አምነዋለው ይባላልና በአደባባይ እንደብቅል የተሰጠውን እውነት ለማድበስበስ ስባል ዐይኔን ግምባር ያድርገው ዓይነት ጨወታ በመደመር ዘመን ቦታ የለውምና ልቤ እጄ ንፁህ ነው በሚል የአፍ ካራቴ ሳይሆን በህጋዊ አካል በህጋዊ መንገድ በሚደረግ ምርመራ ብቻ ንፁህ ከድፍርሱ ይጣራ። አዎ ማንም ከህግ በላይ አይደለምና አለማወቅንም ሆነ ህገወጥነትን ለተቋሙ ተቆርቋሪ በምያስመስል ጭምብል ውስጥ ሆኖ መሸወድ የማይቻልበት ደረጃ ደርሷልና ህገወጥነት በህግ ይዳኝልን።

ይህ አቤቱታ ማንኛውንም ግለሰብ አስቀድሞ ጥፋተኛ ለማድረግ ሳይሆን እውነታው በማስረጃ እንዲረጋገጥና የሆስፒታሉ የፋይናንስ ሥርዓት በግልጽነትና በተጠያቂነት እንዲተዳደር ለመጠየቅ ነው።

እናም የጥቂት ግለሰቦች ኪስ መደለበያነት ስባል በከፍተኛ ሁኔታ እየባከነ ያለውን የህዝብና መንግስት ሀብት ገንዘብ ለመታደግ ስባል ለሚመለከታቸው አካል በተደጋጋሚ ጥሪው ቢደርሳቸውም ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ምላሽ ስላልተሰጠበት ዛሬም የፊትህ ያለ ጩኼት ይሄው ቀጥሏልና ተጠያቂው ይጠየቅልን።


የሚሰጡ ማስረጃዎች በሕግ በተፈቀደው መጠን ሚስጥራዊ እንዲደረጉና በምርመራው የሚገኙ ማስረጃዎች መሠረት ተገቢው አስተዳዳራዊ ወይም ህጋዊ እርምጃ ይወሰድልን።

አዎ ከጉዳዩ አሳሳብነት አንፃር በገለልተኛና አካላት በማስረጃ ላይ የተመሠረተ አስቸኳይ ምርመራ እንድደረግና ተጠያቂነትም ይሰፍን ዘንድ እንድሁም የመንግስት ገንዘብ ወደ ካዝና ተመልሶ ለህዝብ ጥቅም እንድውል ብቻ ይህንን አቤቱታ ለሚመለከተው አካል በአክብሮት እናቀርባለን።


ግልባጭ፡-
ለፌደራል ፀረ ሙስና
ለጤና ሚኒስቴር

አባሪ፦ የቀረቡ የሰነድ ፎቶግራፎች


የማስረጃ ፎቶ




የማስረጃ ፎቶ




የማስረጃ ፎቶ




የማስረጃ ፎቶ



የማስረጃ ፎቶ



የማስረጃ ፎቶ



NO	Name	proffession	monthly fee	per hour fee	total hour	duty fee per month
1	Dr.HGebrrel Gettachw	GP	19,464.00	81.10	544.00	44,118
2	Dr Adane Asefa	GP	19,464.00	81.10	370.00	30,007
3	Dr Belachew Bereta	GP	21,238.00	88.49	300.00	26,547
4	D/R Tilahun Dawite	GP	21,238.00	88.49	300.00	26,547
5	D/r Lideya Desta	GP	19,464.00	81.10	370.00	30,00
6	Menegesetu Mazhgo	GP	19,464.00	81.10	370.00	30,00
7	D/r Amsalu Petros	GP	19,464.00	81.10	370.00	30,00
8	D/r Hailie Markos	GP	19,464.00	81.10	370.00	30,00
9	Dr Nuraid Dagmawi	GP	19,464.00	81.10	300.00	24,33
10	D/r Yonas Asgiehw	GP	19,464.00	81.10	300.00	24,3
11	D/r Temesgen Gerumchew	GP	19,464.00	81.10	300.00	24,3
12	D/r Dira Dita	GP	19,464.00	81.10	300.00	24,3
13	Dr Evobe Elias	GP	19,464.00	81.10	300.00	24,3
14	D/r Milineti Boke	GP	23,173.00	96.55	300.00	28,9
15	Ato Bekachew Workneh	HO	21,238.00	88.49	248.00	21,9
16	W/ro Meseret Mulu	Biomedical	13,732.00	57.22	250.00	14,3
17	Ato Tinsaye yenene	Biomedical	14,983.00	62.43	250.00	15,6
18	Ato Asimiil Gebeta	HO	21,238.00	88.49	100.00	8,8
19	Ato Sisay Chaliw	HO(Liaison)	23,173.00	96.55	200.00	19,3